# አብዮታዊት ኢትዮጵያ ፫

★ የጋራ ግንባር

★ ንቃተ ህሊና

★ የወዝ አደሩ ፓርቲ

★ ፓርቲ

ግንቦት ፴ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም.

ርእሰ አንቀጽ

# የትግል ግንባር

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወደቀበት አዘቅት ወጥቶ አዲስና የተሟላ ኑሮ ይጠይቃል፡፡መብቱም ነው በሀብታምና ለምለም ሀገር ውስጥ ላቡን አንጠፍጥፎ የሚኖር ታታሪ ሕዝብ ከድኅነት፤ከርኃብና ከድንቁርና ጨለማ ጨርሶ የተፍታታና የተሟላ ኑሮ መኖር ይገባዋል ፡፡ ለዚህም ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቀንደኛ ጠላቶቹ ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም በምጽዋት የጠየቀውና የሚጠይቀው ሌላ ነገር የለውም ፡፡ ነፃነቱ ፤ ክብሩ ፤ አንድነቱና ሰብአዊ መብቱ ታውቆለት በሰላም ወደሚኖርባት አዲሲቱ ኢትዮጵያ በሚያደርገው ጉዞ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከዛሬ በብዙ መሥዋዕትነት የተወጣው የትግል ታሪክ እንዳለው ሁሉ ወደፊትም ገና ብዙ መሥዋዕትነት እንደሚጠብቀው ያውቃል ፡፡ ዝግጁም ነው፡፡

ይህ የቆየ የነፃነት ተጋድሎ በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ፈንድቶ ሀገራችን በአብዮታዊ ማዕበል መንቀልቀል ከጀመረችበት ወቅት አንስቶ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በደመኛ ጠላቶቹ ላይ ብዙ ድሎችን ተጎናጽፏል ፡፡ ቢሆንም በተናጥል የተገኙት ታላላቅ ድሎች በተቀነባበረና በማያዳግም ሁኔታ ሊረጋገጡ የሚችሉት በፊውዳሊዝም ፤ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም መቃብር ላይ በመሆኑ ወደዚህ ግብ የሚደረገው ግስጋሴ ለአድኃሪ ኃይሎች አንዳችም ፋታ ሳይሰጥ ወደፊት መጓዙት ይኖርበታል ፡፡

ነገር ግን አብዮታዊ ትግላችን ግቡን እንዲመታ በየጊዜው ወዳጅና ጠላትን በሚገባ መለየት፤ ወዳጅን በሙሉ መሰብሰብና ማጠናከር ፤ ጠላትን ደግሞ መበተንና ማድከም ያስፈልጋል ፡፡ በመሐል ደግሞ በመደባዊ አቋማቸው የተነሳ ከበዝባዥም ከተበዝባዥም በመጥቀስ የሚያወላውሉትን መሐል ሰፋሪ ኃይሎች አረጋግቶ ወደ አብዮቱ ለመሳብ መታገል ያስፈልጋል ፡፡

ይህንን የትግል ስልት ከሥራ ላይ ለማዋል የአብዮቱ ኃይሎች በሙሉ ዓላማችን ብለው የሚያተኩሩበት አቅጣጫና የሚተባበሩበት የጋራ መድረክ ያስፈልጋል ፡፡ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም» በሀገራችን የሚገኙ ፀረ—ፊውዳል ፀረ—ኢምፔሪያሊስትና ፀረ—ቢሮክራቲክ ኃይሎች የጋራ በሆነ ዓላማ ላይ የሚሰበስብ ፕሮግራም በመሆኑ በኢትዮጵያ ጭቁኖች የነፃነት ታሪክ ውስጥ የማይናቅ ቦታ ይኖረዋል ፡፡ ይህ ከኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁኔታ የፈለቀ አብዮታዊ ፕሮግራም እፍኝ ከማይሞሉ ፀረ—ሕዝብ ኃይሎች በስተቀር የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም የሚያንጸባርቅ ፕሮግራም ነው ፡፡

ነገር ግን ከዚህ በፊት እንዳልነው ይህ ፕሮግራም ከዘጠና በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ያለው ፕሮግራም በመሆኑ ብቻ ካለትግል ከሥራ ላይ አይውልም ፡፡ ስለሆነም የዚህ ፕሮግራም ደጋፊዎች በሙሉ ትግላቸውንና ጥረታቸውን ሁሉ የሚያቀነባብሩበት አንድ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ያስፈልጋቸዋል ፡፡

ይህ የትግል ግንባር ሕዝባዊ መሆን አለበት ፡፡ ማለትም በዛሬው ወቅት ፊውዳሊዝምን ፤ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን የሚቃወሙትን የሰፊው ሕዝብ ወገኖች በሙሉ ማቀፍ ማስተባበርና መምራት አለበት ማለት ነው ፡፡ ይህ ግንባር በርግጥ ሕዝባዊ ግንባር እንዲሆን የመደቦችንና የኅብረተሰብ ክፍሎችን ቁንጮዎች ሳይሆን ገበሬዎችን ፤ ወዝአደሮችን ፤ ጭቁን ወታደሮችን ፤ ሴቶችን ፤ ወጣቶችን ፤ ምሁራንን ፤ ልዩ ልዩ ባለሙያዎችን ፤ አስተማሪዎችን ፤ ነጋዴዎችን - - - - ባጭሩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም የነፃነት ፤ የእኩልነት ፤ የብልጽግናና የእርምጃ ተስፋ የሰጣቸውን ኃይሎች በሙሉ ማንቀሳቀስ መቻል አለበት ፡፡



እነዚህ የተሰበጣጠሩና ከተወሰነ ደረጃ በኋላ የተለያየ ዓላማ የሚኖራቸው ኃይሎች በተናጠል የሚመለከታቸውን ጥቅም ለማስከበርና በጋራ የሚመለከታቸውን ትግል ለማስተባበር የሚችሉት አስቀድመው በፈርጅ በፈርጃቸው ተደራጅተው ሲገኙና አብዮታዊ ግንባር ሲፈጥሩ ብቻ ነው ፡፡

ይህ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር በሚልዮን የሚቆጠሩትን የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ሊያንቀሳቅስና ሊመራ የሚችለው ሕዝብ በሞያ ድርጅቶች ፤ በሕዝባዊ ድርጅቶችና በፖለቲካ ፓርቲዎች አማካይነት በየደረጃው ለመደራጀት ሲችል ነው ፡፡

የምናቋቁመው ግንባር ጥንካሬና የአመራር ጥራት የሚወሰነው እነዚህ በውስጡ የሚገኙት ልዩ ልዩ ድርጅቶች ራሳቸው አስቀድመው ጠንካራና ጥራት ያላቸው ሲሆኑ ነው ፡፡ ግንባሩ ዲሞክራሲያዊ የሚሆነውም ያቀፋቸው ድርጅቶች ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሲሠሩ ብቻ ነው ፡፡ ሰፊውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንቀሳቀስ የሚችለው እነዚህን ድርጅቶች ሕዝቡ ያቀፋቸው እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ፀረ—ፊውዳልና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ተባብረው ስለሚያቋቁሙት ግንባር ድርድር ከመጀመራቸው በፊት በየፈርጃቸውና በየደረጃው ለዚህ ግንባር መሠረት ሊሆኑ የሚችሉትን ጠንካራና ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ለመመሥረት መታገል አለባቸው ፡፡

የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊ ድል ቁልፍ የያዘው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ባፋጣኝ መቋቋም ይኖርበታል ፡፡ ወደዚህ አብዮታዊ ግንባር በሚደረገው ትግል የጊዜው ዋናና አጣዳፊ ተግባር የወዝአደሩን ፓርቲ ፤ ሌሎች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎችን ፤ የሞያ ድርጅቶችንና ሕዝባዊ ድርጅቶችን በጠነከረ መሠረት ላይ ለማቋቋም መታገል ነው ፡፡

በዚህ መልክ የሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩ መሠረት ከተጣለ በኋላ እነዚህ ፓርቲዎች ፤ የሞያና ሕዝባዊ ድርጅቶች ወኪሎቻቸውን ወደ አገር አቀፍ የግንባሩ መመሥረቻ ጉባኤ መላክ ይችላሉ ፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ ስምምነት በሚደረስበት መዋቅር ፤ የትግል ፕሮግራምና ታክቲክ ተመርኩዞ በእርግጥ መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚወክልና ትግሉን የሚመራ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ይቋቋማል ፡፡

የኢትዮጵያ ጭቁኖች በሙሉ በአንድ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር መሰብሰብ ከፍተኛ ትግልንና መሥዋዕትነትን የሚጠይቅ ተግባር ነው ፡፡ ነገር ግን በተበታተነ ትግል የተደራጁ አድኃሪዎችን መደምሰስ እንደማይቻል እናውቃለን ፡፡ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ከከተቷቸው አዘቅት ሊወጡ የሚችሉት በመራራ ትግል ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው ፡፡ ያልተደራጀ ትግል ደግሞ ምንም ያህል ቆራጥ ቢሆን ዘላቂ ድልን አያስገኝም ፡፡ የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ የእውነተኛ ሰላም ፤ ነፃነት ፤ አንድነትና ብልጽግና ቁልፍ የተያዘው በዚህ በአንድነት ሆነን በምንመሠርተው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ነው ፡፡ ስለሆነም የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ታሪካዊ ኃላፊነታቸውን በመቀበል ለትግል ለትግል ይህንን አብዮታዊ ግንባር መፍጠር ይገባቸዋል ፡፡

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው

« አብዮታዊት ኢትዮጵያ »